DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of the Chancellor

መስከረም (September) 2016

ውድ የዲሲፒኤስ ተማሪዎች ወላጆች፤

በአለፈው ሣምንት፣ የስቴቱ የትምህርት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ  ጽሕፈት ቤት (OSSE)፣ ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ ለኮሌጅ እና ለሙያ ዝግጁነትን በቅንጅት በሚገመግመው በ (PARCC) ፈተና የተማሪዎችን ውጤት አውጥቷል። በመጭዎቹ ሣምንታት፣ ከ OSSE ስለ ልጅዎ ግላዊ የፈተና ውጤት ነጥቦች አጠቃላይ ሁለ አቀፍ ሪፖርት ይድረስዎታል።

በአለፈው ዐሥር ዓመት፣ ዲሲፒኤስ የምሩቃንን መጠን እና የላቀ የምደባ ነጥቦች ከመጨመር አንሥቶ እስከ የተመዝጋቢዎችን ቁጥር ከፍ ለማድግረ እና የተማሪዎችን የእርካታ መጠን ከፍ እስከ ማድረግ ድረስ፣ ዲሲፒኤስ በእያንዳንዱ የስኬታማነት መስፈርት ሁሉ ቀጣይነት ያለው የማያቋርጥ ጭማሪ አሳይቷል። በዚህ ዓመት የዓመቱ መሻሻል፣ ዲሲፒኤስ ትክክለኛውን ጥረት እያደረግን መሁኑን ያመለክታል። በመምህራን እና በትምህርት ቤት መሪዎች ላይ ያለን ትኩረት፣ ከወል ነጥቦች ጋር የተጣጣመ ሥርዓተ ትምህርት እና ወላጆችን እና ማኅበረሰቦችን በሥራ የሚያሳትፍ ተግባር እየሠራ ነው።

የ PARCC ውጤቶቻችን፣ በትክክለኛው ጎዳና ላይ እየተጓዘን ለመሁኑ አንድ ተጨማሪ አመልካች ይሰጠናል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎ ቻችንን ሁሉ ለኮሌጅ እና ለሙያ እያዘጋጀናቸው መሆናችንን እርግጠኛ ለማድረግ ገና በርካታ ሥራዎች መሥራት እንዳለብን ያመለክ ታሉ። የ PARCC ፈተና የተቀየሰው፣ በተለይ ተማሪዎች ለወደፊት ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጓቸውን ክህሎቶች ለመለካት ነው። ያንኑ ተመሳሳይ ግብ በአእምሮ በማስቀመጥ ሥርዓተ ትምህርታችንን እና የመምህራን ሥልጠናችንን ጨምሮ፣ ከእያንዳንዱ ልጅ ለስኬ ታማነት የሚያስፈልጉትን ክህሎቶችን እንዲጎናጸፍ ለማድረግ ከሚያስችል ሁኔታ ጋር ጥረቶቻችን እንዲጣጣሙ አድርገ ናል። በዚህ መሠረት የ PARCC ፈተና ውጤቶቻችንን፣ሥልቶቻችን አመርቂነት ባለው ሁኔታ ተማሪዎቻችንን ለወደፊት ብሩህ ሁኔታ እያዘጋጃቸው መሆናችንን ለመገምገም ልንጠቀምበት እንችላለን። በእነዚህ ውጤቶች የሚታይ ግልጽ ሲሆን ይኸውም በትክክለኛ ሥል ቶች እየተጠ ቀምን መሆናችንን እና አሁንም ቢሆን ገና ብዙ የበለጠ መሥራት እንዳለብን የሚያመልክት ነው።

እንደ ወላጅ የተማሪዎን የ PARCC ፈተና ውጤቶች እንዲመለከቱ እና የሚከተሉትን ዐይነት ተመሳሳይ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ አበረታ ታለሁ። ተማሪ ልጄ ለወደፊት ስኬታማነት በፈር ላይ ነው ወይ ያለው? ጥናካሪዎቹ ምንድን ናቸው? ተፈታታኝዎቹስ? የእድገት እርምጃ ዎችን እያደረገ መሆኑን ቀጣይ ለማድረግ በምን ላይ ነው ትኩረት ማድረግ ያለብን? በእርግጥ እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ለመመለስ በ PARCC የፈተና ውጤቶች ብቻ አይደለም መጠቀም ያለብዎት። ስለ ልጅዎ ሥራ የተካተተ እና የተሟላ ሥዕል ለማግኘት፣ የክፍል ትም ህርት ውጤቶችን እና የመምህሩን የጥንቅር ውጤቶች ነው መመልከት ያለብዎት።

እኛ ተመሳሳይ ግቦችን እንጋራለን። ልጆቻችን ለስኬታማነት የሚያስፈልጉቸውን ክህሎቶች እየተቀናጁ እያሉ ተማሪዎቻችንን በትምህ ርት ቤት የበለጸጉ ልምዶች እንዲቀስሙ እንፈልጋለን። የ PARCC ፈተና ውጤቶች፣ ይህንን ግብ እየጨበጥነው እንደሆነ ለማየት የሚያ ስችል አንድ መረጃ ይሰጠናል። እኛም እንደርስዎ የልጆቻችንን የወደፊት የስኬታምነት እድል ከፍ ለማድረግ በመረጃዎች ሁሉ እንጠ ቀማለን።

በጋራ በምናደርገው ስኬታማነታችን ኩራት የሚሰማኝ ሲሆን፣ በልጅዎ ትምህርት አኳያ እርስዎን እንደ አጋር ተጓዳኝ በመያዜ ከፍ ያለ ኩራት ይሰማኛል።

ከአክብሮት ጋር፣

Kaya Henderson
ቻንስለር፣ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Chancellor, DC Public Schools)